# PANORAMA # XVIII

## የትዝብት አድማስ

መጋቢት 12 2000

## የኋላ ኋላ ወደ ሕዝብ ጎራ መቀላቀል የታሪክ ግዴታ ነው።

አሮጌ አምባገነን ሄዶ አዲስ አምባገነን በተተካ ቁጥር÷ አንድ አንድ የኅብረተስብ ክፍሎች፣የመጣው ከሄደው ይሻል ይሆናል በሚል ቀቢፀ ተስፋ፣ እስኪ ለዚህኛው ደግሞ ትንሽ ጊዜ ሰጥትን እንየው-እንፈትሸው እንታዘበው ማለታቸው ያልተለመደ አልነበረም። ይህን ማለታቸው ምንአልባት ካለፈው የተሻለ ሁኔታ ሊያመጣ ይችል ይሆናል ከሚል በመነሳት፣ "ያለፈው መከራ የሚመጣው ደስታ ይሆንልን" ከሚል ባህላዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።ይህ እራስን የማፅናናት ተስፋ ደግሞ በሰው ልጆች ባኅርይና ልምድ የቆየ ነው። መቸም የማነኛው አምባገነን ሥርዓት ቋሚ ባኅርይና ድርጊት ያው ዞሮ ዞሮ ተመሳሳይ በመሆኑ፣ የሀገሪቱ ሁኔታ ቀስ በቀስ ከእሳቱ ወደ ረመጡ ሲለወጥ፣ ሕዝቡ "አየ ትሻልን ሰድጄ ትብስን አመጣሁ" ማለቱን ይቀጥላል። እሳትና ረመጥ የሚፈራረቅበት ሕዝብ ደግሞ፣የተሻለ ሁኔታ በማያደጋግም መልኩ፣ በሚያስተማምንና በዘለቄታው ሁኔታ እስከሚያረጋግጥ ድረስ፣ሁሉንም አማርሮ አማርሮ ተስፋው ሲሟጠጥበት፣ ያው እንደተለወደው ባኅላዊ አነጋገር፣ "የአርባ ቀን ዕድሉን " እያማረረ የመከራ ሕይትወቱን ይገፋል ። ሕይወት እራሷም የተፈጥሮ ህግ በሚቀይስላት ጎዳና መጓዟን ትቀጥላለች። አዲሱ አምባገነን ሥርዓትም በአፍላው መጨቆኑን እየቀጠለ ይጓዛል። " ሎሌ በአፍላው የአህያ መኸገር ይከላል" እንደሚባለውም፣ አዲሱን አምባገነን ሥርዓት ለማገልገል በርካታ አፍለኛ አገልጋዮች በአዲስ ጥርስ ለመጋጥ በየቦታው እንደ ጅብ ተጠራርተው ብቅ ብቅ ይላላሉ። ሕዝቡም አዲስ የጨላማ ኑሮውን ይቀጥላል። ባተሌዎች እንደሚሉትም "ውሾቹም ይጮኻሉ፣ ግመሉም ይጓዛል" አዝማሪዉም፣ " አንች እንደምን አለሽ፣ እኔ እንዳለሁ አለሁ፣ ስቃይ ተሸካሚ አጋሰስ ሆኛለሁ"እያለ በዘለሰኛ ግጥሙ ኅብረተሰቡን ያስተዛዝናል÷ ያፅናናል።

ማነኛውም አምባገነ ሥርዓት ምን ጊዜም ቢሆን ፣ምንም ቢለፋ ቢደክም፣ የሕዝቡን ድጋፍና አመኔታ ስለማያገኝ የሥልጣን ጊዜውን ሊያራዝም

የሚችለው፣
የቢሮክራሲውን፥ የወታደሩን፥ የስለላ መዋቅሩን፥የፕሮፓጋንዳ አውታሩንና የገንዘብ ምንጩን በመዳፉ በማስገባት ነው። በነኝህ መዋቅራት ውስጥ የተካቱት ግለሰቦች ሁሉ፣ በሥርዓቱ አመኑበትም አላመኑበትም፣ በግድ መኖር ስለሚኖርባቸው፥ ቤተሰቦቻቸውንም የመደገፍ ኃላፊነት ስላለባቸው፣ የአምባገነኑን ሥርዓት ማገልገሉን ይቀጥሉበታል።

ለዚህም ነው፦

"አወይ ልጅ ማሰሪያው አወይ ልጅ ገመዱ፥

ጎጆማ ምን ይላል? ጥለውት ቢሄዱ። " ሲባል የነበረው !

በመሆኑም በሥርዓቱ ቀጣሪነት የሚሠሩ፣ ሐኪሞች፣አስተማሪዎች፣ዳኞች፣ የቢሮ ሰራተኞች ወዘተ.. መኖር ስለአለባቸው ብቻ ሳይሆን ፣ ቤተሰቦቻቸውንና ልጆቻቸውን ለመደገፍ ይገደዳሉ። በመሆኑም የሥርዓቱ ተቀጣሪዎች በመሆናቸው ብቻ፥ መላው ሕዝብ የአምባገነኖች አካልና አምሳል አድርጎ ሊቆጥራቸው አይችልም። ተገቢም አይደለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ለማመዛዘ አስተዋይነቱ ብቻ ሳይሆን፥ ንቃተ ኅሊናውም የሚፈቅድለት መሆኑን እናምናለን። የሲቪል ሰራተኛው ቀርቶ፣ ወታደሩም ቢሆን ዓይነተኛ ሙያው፣ ተልዕኮውና ግዳጁ በመጀመሪያ የሀገሩን ዳር ድንበር ከአጥቂ ጠላት መከላከል ስለሆነ፣የአምባገነኖችን የወንጀል ትዕዛዝ ለመፈፀም ሲል አፈ- ሙዙን ወደሰላማዊው ሕዝብ እስካላዞረ ድረስ፣ ወገንተኝነቱና ታማኝነቱ የሕዝብና የሀገር መሆኑን ምልተ-ሕዝቡ በሚገባ ይረዳለታል። ይህ መሠረታዊና ዘለቂታዊ ቃልኪዳን በሕዝቡና በወታደሩ መካከል ሊኖር የሚገባው እንደሆነ ሁሉም ይረዳለታል። ይደግፈዋልም። ምናልባት አንድ ቀንም ሲመቸውከአምባገነኖች ጭቆና ወገኖቹን ነፃ የሚያወጣ በት ቀን ይመጣል ተብሎም ይጠበቅበታል። ይህንን ስምምነትና መግባባት የማይፈልጉት አምባገነኖችና ሥርዓታቸው እንዲቀጥል የሚፈልጉ ንዑናን የአገዛዙ አባላት ብቻ ናቸው። ይህ ማለት ግን የወታደር መለዮ የደፋው ሁሉ የአምባገነኖች የመጨቆኛ መሳሪያ አይሆንም ማለት አይደለም። እንደ ሂትለሩ የናዚ ፓርቲ የብናማ ሸሚዝ ለባሽ ወታደሮች፥ ወይም ደግሞ

እንደ ሙሶሊኒው የፋሽስት ፓርቲ ጥቁር ሸሚዝ ለባሾች ሁሉ፣ የወያኔዎቹ የአጋዚና የፌዴራል ነፍሰ ገዳዮችም የነመለስ ዜናዊ የሕዝብ ጨፍጫፊ ዘረኛ ፋሽስቶች እንዳሉም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሰወር አይደለም። እነዚህ ፈጥኖ ደራሽ የሞት መልዕክተኞች የንፁኃን ኢትዮጵያውያን/ት የጓጎለ ደም

በእጃቸው እንዳለ በመገንዘብ፥ ከዚህ ብሔራዊ የወንጀል ድርጊት መራቅ ይኖርባቸዋል። እለዚያ፣

" በወልወል በረሃ ያባቶቻችን ደም ጥንት እንደፈሰሰው፥

በግራሲያኒ ትዕዛዝ የካቲት 12 የወገናችን ደም ወርዶ እንደጎረፈው

ዛሬም በወያኔ አጋዓዚ የኢትዮጵያውያን ደም መሬቱን አራሰው።"

እየተባለ በታሪክና በመጭው ትውልድ ዘንድ የሚዘመርባቸው መሆኑን የወያኔ መሪዎች እንዲገነዘቡት እናሳስባቸዋለን ።

በአንድ የአምባገነን ሥርዓት ውስጥ በሚከሰት እንቅስቃሴ ሊጠን የሚያስፈልገውና ሊፈረጅ የሚገባው ብሎም በየመልኩ እየታየ መቀመጥ ያለበት፣የሥርዓቱ ፖሊሲ አውጭዎችና ፣ ተርጓሚዎች በጠቅላላው የጨቋኙ ሥርዓት አራማጆች በመሆን በግልፅም ይሁን በስውር ሕዝብ የሚበድሉ ሀገር የሚጎዱ እነማን መሆናቸውን ለይቶ ማወቁ ነው። እነኝህ ክፍሎች እያዩ፣ እየሰሙና እያወቁ ሆን ብለው የአምባገነኖች እጅና እግር፣ ዓይንና - ጆሮ በመሆን የሥርዓቱ አንድ አካል አንድ አምሳል በመሆን በጭቆናው፣ በማሰቃየቱ፣ በግድያው፣ በዝርፊያውና በቅሚያው ውስጥ አባሪ ተባባሪ የሆኑትን ግለሰቦች ለይቶ ማወቅ ተገቢ ነው። ፍርድ በማጣመም ፍትኅ-ርትዕ ያጎደሉ በሙስና የተዘፈቁ፣ ዜጋን ከዜጋ ጋር በማጣላት ሕዝብ ያፋጁ ሁሉ በዚህ ሁሉ ክፍል ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው። እነኝህ ክፍሎች ከአምባገነኑ ሥርዓት ጋር በመወገን ሕዝብንና ሀገርን የሚጎዱት፣ አላፊ ጠፊ ለሚሆነው የከንቱ ጥቅም ማስገኛ ለሚሆነው ለሹመት ሽልማት፣ ለሀብት - ንብረት ተገዥዎች ስለሚሆኑ ብቻ ነው። ይህንን ዓይነተኛ ዕውንታ የተገነዘበ ኅብረተሰብ፣ ጠላት ወዳጁን ለይቶ ስለሚያውቅ በአንድ አምባገነን ሥርዓት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራውን ማንኛውም ሰራተኛ ሁሉ በደፈናው በአንድ አይነት ሚዛን አይመዝነውም። በተለይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አዙሮ የሚያይበት ረዥም አንገት ያለው በመሆኑ በአገዛዙ ውስጥ ማን? ምን ? እንደሆነ አንጥሮ-አብጠርጥሮ ያውቀዋል። በመሆኑም፣ ዛሬ በዘረኞች አምባገነን አገዛዝ ውስጥ የሚያገለግለው ሁሉ የሕዝብ ደመኛ የሀገር መጋኛ ነው ብሎ አይቃወምም። ምክንያቱም የዚህ ዓይነት አስተሳሰብና ዕምነት በመሠረቱ ስህተት በመሆኑ ነው።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሰውን መሠረታዊ ቁም ነገር በግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ከተቻለ፣ ከኀልፈተ- አምባገነን ሥርዓት በኋላ ለሚመጠው

ሁለንተናዊ ዕውንታ፥ ሁሉም በበኩሉ ሊያስብበትና ሊጨነቅበት ይገባል:: ከሁሉ አስቀድሞ፣ ማነኛውም ዜጋ በአንክሮ ሊገነዘበው የሚገባው ቁም ነገር፣ ሕዝብ ፣ሀገር፣ ታሪክና ትውልድ፣ መሠረተዊ መሆናቸውን ነው:: በአንፃሩ ደግሞ፣ መንግሥትና ማነኛውም ሥርዓት በተለይም አምባገነን ሥርዓት እንደ ጤዛ የሚረግፍ እንደ ጥላ የሚያልፍ መሆኑን መረዳት ከአስተዋይ ሕዝብ የሚጠበቅ ባኅርይ መሆኑን ነው:: አምባገነኖች በሥልጣን ዘመናቸው ለሥርዓቱ አገልጋዮቻቸው፣ በልተው ሊያበሉ፣ተጠቅመው ሊጠቅሙ፥ ሹመው ሊሽልሙ፣ ዘርፈው ሊሰጡ፣ ሌላም ሌላም ጥቅማ ጥቅሞች ሊለግሱ ይችሉ ይሆናል:: ሦስቱም ተፈራራቂ አገዛዞችያደረጉት ይኸንኑን ነው:: ሥርዓቱ ሲገረሰስ ግን አምባገነኖች ከሕዝብ ፍርድ ለማምለጥ ሲፈረጥጡ፣ የመጨቆኛ መሳሪያዎቻቸው ሲፈራርሱ፣ የስለላ መረቦቻቸው ሲበጣጠሱ፣ ተከታዮቻቸውን አውላላ መዳ በትነዋቸው እንደሚሄዱ የቅርብ ትዝታ ነው:: ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነውና የመያስተዛዝበው ግን ለሀገር መከላከያ ታስቦ የሰለጠነው፣ የተደረጃውና የታጠቀው ከፍተኛ የሀገሪቱ ሀብት የወጣበት ሠራዊት በከንቱ መበታተኑና ምናልባትም ወደፊት በተመሳሳይ መልኩ ይህ ዓይነት ክስተት ሊመጣ የሚችል መሆኑ ነው::

ዛሬ በወያኔ የዘረኛ አገዛዝ ስር ያለው የሀገር መከላከያ ሠራዊት ከሁሉ አስቀድሞ ሊያውቀው የሚገባው መሠረታዊ ግዴታ እንዳለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ይገነዘበዋል:: ያምናልም:: ይኸውም የመለስ ዜናዊና የግብረ-አበሮቹ የግፍ አገዛዝ አስፈጻሚና ተባባሪ ከመሆን እንዲቆጠብ ነው:: የሙያው ምግባረ-ሰናይም ይሁን የተመሠረተበት ዓላማ፣ የቆመበት ተልዕኮ የሚነግረው፣ ምን ጊዜም ቢሆን ፣ ለሕዝብና ለሀገር የቆመ መሆኑን እንጅ የአምባገነን አገዛዝ የጭቆና መሳሪያ አለመሆኑን ነው:: የወያኔን መሪዎች ዓላማና ድርጊት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ስለሚያውቀው፣ የመከላከያ ሠራዊቱም የሕዝቡን የልብ ትርታና ሰቆቃ በሚገባ ሊረዳው ይገባል:: በመሆኑም ጊዜው ሳይመሽ ከአሁኑ የሕዝብ አለኝታ፥ የሀገር መከታ መሆኑን በተግባር ማሳየት ይጠበቅበታል::

የወያኔን የጥፋት ጎዳናን ለመግታትና ሀገሪቱንም ከጥፋት ለማዳን በሚደረጉት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ጣልቃ በመግባት የሰላማዊ ዜጎችን ደም ከማፍሰስ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ፣ በአንፃሩ ግን፣ የወያኔ ወንጀል አባሪ ተባባሪ በመሆን የጥፋት መልዕክተኛ እንዳይሆን መርሳት እንደሌለበት ነው::ይህንን በመዘንጋት እጁን በንፁኃን ዜጎ ች ደም ከበከለ፣ በታሪክና በህግ ፊት ተጠያቂ ከመሆን የማያመልጠ መሆኑን ለደቂቃም ቢሆን ሊስተው አይገባም:: ለሀገር መከላከያ ሲባል የታጠቀውን የጦር መሳሪያ አፈሙዝ ወደ ወገኑ ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ማዞር

የለበትም፡፡ ይህ ተግባር የባዕዳን ባላንጣዎችና የሀገር በቀል የኢትዮጵያ ጠላቶች የእነወያኔ እንጅ የኢትዮጵያ መከላካያ ሠራዊት ግዳጅና ተግባር አይደለም፡፡ በመሆኑም ታሪካዊ ግዳጁን መወጣት የሚችለው፣ ከትውልድና ከታሪክ ወቀሳ እንዲሁም ከፍርድ ቅጣት ነፃ ሊወጣ የሚችለው፣ የዘረኞችን ዓላማና አጀንዳ ለማስፈፀም ሲባል በሕዝብ ላይ የጠላትነት ተግባር ከመፈፀም ሲታገድ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣በወያኔ የስለላ መዋቅር ውስጥ ገብታችሁ፣ ጨለማን ተገን አድርጋችሁ፣ የአፋኝ -ፈንጋይ ወንጀል የመትፈጽሙ ሁሉ፣ ከዚህ የአፋኝና የነፍሰ-ገዳይ ሥራ ተወግዳችሁ የሰላማዊውን ሕዝብ ሰቆቃና ግፍ እንዳታበረክቱት የኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠይቃችኋል፡፡ይማፀናችኋልም፡፡በአሁኑ ወቅት አንድ አንድ የፀጥታ ሰራተኞችና በልደረቦቻችሁ በሚሰራው የግፍ ተግባር በመፀፀት የወያኔን ሥርዓት እየረገሙ ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ጎራ እየተቀላቀሉ መሆናቸው የሕዝባቸውን መከራና እሮሮ እያቃለሉለት በመሄድ ላይ ናቸው፡፡ ሌሎቹም የዘረኛው አገዛዝ አባሎች እራሳቸውን ከተጠያቂነት ለማውጣት የሕዝቡ ወገን መሆናቸውን ለመግለፅ ልዩ ልዩ ውሳኔዎች በመውሰድ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ እንደትክክለኛ ርምጃ እየተወሰደላቸው ነው፡፡ ማንም ማን ቢሆን፥ የማታ ማታ ወደ ሕዝብ ጎራ መቀላቀሉ አይቀሬው የታሪክ ህቅ ነው፡፡

አምባገነኖች ሲያልፉ ሲጠፉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ፤ ከታሪኩ፣ ከነፃነቱና ከአንድነቱ ጋር ለዘለዓለም በሠላምና በልማት፣ በብልፅግናና በደስታ አብሮ እንደሚኖር ማንም ጠላት፣ እንዲሁም ወያኔና ግብረአበሮቹ ሊጠራጠሩ አይችሉም፡፡